# የቻድ አገር ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ጉብኝት አደረገ

ጥር 16 ቀን 2010 ዓ.ም. በኢንተርናሽናል ፌዴሬሽን ኦፍ ኮንስለር ቻምበርስ ፎር አፍሪካ አስተባባሪነት ከቻድ የተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ማኀበራት፣ እና ከማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ የተወጣጡ 14 የልዑካን ቡድን አባላት በኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ጉብኝት አደረጉ። ለልዑካን ቡድኑ የኢንስቲትዩቱ የጫማና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ኃይለኪሮስ ደበሳይ አቀባበር ያደረጉላቸው ሲሆን ስለኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ በአጠቃላይና ስለኢንስቲትዩቱ በተናጠል የተዘጋጀ ገለፃ ተደርጓል።

የልዑካን ቡድኑ በተደረገው ገለፃ ስለኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ በቂ እውቀት እንዳገኙና እንደተደነቁበት ገልፀው አፍሪካ አገሮች በኢንስቲትዩቱ እንዲጠቀሙ በኢንስቲትዩቱ በኩል ምን እየተሠራ እንዳለና እነሱ በምን ዓይነት መንገድ በኢንስቲትዩቱ ሊደገፉ እንደሚችሉ ጥያቄ አቅርበዋል። በዚህም መሠረት ኢንስቲትዩቱ መላው አፍሪካ አገሮች በዘርፉ በጋራ አድገው በዓለም ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንደሚሠራና ከዚህ ቀደምም ከሱዳን፣ ከታንዛንያ፣ ከቦትዋናና ከደቡብ አፍሪካ ባለሙያዎች ወደኢንስቲትዩቱ መጥተው ሰልጥነው መመለሳቸውን እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችም በእነዚህ አገሮች ሄደው ለባለሙያዎች ስልጠና እንደሰጡ እንዲሁም በቅርቡም ከተለያዩ አገሮች ባለሙያዎች በኢንስቲትዩቱ ለመሰልጠን እንዲመጡ ስምምነት ላይ መደረሱን በመግልጽ ከቻድም ጋር አብሮ ለመስራት ኢንስቲትዩቱ ፈቃደኛ መሆኑን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

የልዑካን ቡድኑ የኢንስቲትዩቱን ሞዴል ፋብሪካዎች፣ የምርት ልማት ማዕከላት፣ የምርምርና ፍተሻ ላቦራቶሪዎችን ተዘዋውረው የጎበኙ ሲሆን ባዩት መደሰታቸውንና ወደአገራቸው እንደተመለሱም በመንግስት ለመንግስት ግንኙነት በኢንስቲትዩቱ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችሉ ለማድረግ እንደሚሠሩ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።